**Ethiopian Journal of Business and Social Science**

**DOI:** *https://doi.org/10.59122/ 134F59mt*

**Volume: 5 Number: 2 , 2022 , Pages: 89~113**

**ISSN:2707-2770**

# የማጠቃለል ብልሃትን መጠቀም በአማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተጽዕኖ

**[1]አራጋው ሺባባው፣ [2]አገኜሁ ተስፋ፣ [3]ማረው ዓለሙ**

[1, 2]ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ማኅበራዊ ሳይንስና ሥነሰብዕ ኮሌጅ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል፣ aragawshibabaw@gmail.com፤ agetesfa@gmail.com

[3]ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋካልቲ marewalemu@gmail.com

*Article Info*

Accepted on September, 2022

Published on: December, 2022

©*Arba Minch University, all rights reserved*

***አሕጽሮተጥናት***

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ የማጠቃለል ብልሃትን መጠቀም በአማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ መመርመር ነው፡፡ የጥናቱ ስልት ፍትነትመሰል ባለቁጥጥር ቡድን ቅድመፈተና-ድኅረፈተና ነው፡፡ ለዚህም በጎንደር ከተማ የአጼ በካፋ አንደኛ ደረጃ ትምህርትቤት በ2015 ዓ.ም በመደበኛ ክፍላቸው የሚማሩ የ7[1] (ብዛት- 51)ና የ7[3] (ብዛት-51) ክፍል ተማሪዎች በተራ የዕጣ ንሞና በሙከራና በቁጥጥር ቡድን ተሳትፈዋል፡፡ የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ አንብቦ የመረዳት ፈተና ነው፡፡ በዚህም አስቀድሞ ቅድመትምህርት መረጃው ከተሰበሰበ በኋላ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በማጠቃለል ብልሃት የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በመደበኛው ሥርዓተትምህርት ብልሃት መሠረት ማንበብን ለ12 ሳምንት፣ በሳምንት ለአንድ መደበኛ ክፍለጊዜ ከተማሩ በኋላ የድኅረትምህርት መረጃው ተሰብስቧል፡፡ ቅድመትምህርት ረጃዎቹና ፆታ በአበር ተላውጦነት ቁጥጥር ተደርጎባቸው፣ የድኅረትምህርት መረጃው በአበርተኮር መዋቅራዊ የትንተና ሞዴል ተተንትኗል፡፡ በ95% ናሙና አካይ የመተማመኛ ደረጃ (bootstrap confidence interval) የተገኘው ውጤትም ($R^2$=.48 (48%) , $B$=2.72, $S.E.$ =.826, $P$=.001, η2= .25) ሆኗል፡፡ ውጤቱ እንዳመለከተውም የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ማንበብን የተማሩበት የማጠቃለል ብልሃት፣ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ከተማሩበት መደበኛው ሥርዓተትምህርት ብልሃት የበለጠ አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ ጉልህ አዎንታዊ ቀጥተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ ከዚህም በማጠቃለል ብልሃትና አንብቦ በመረዳት ችሎታ መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት መኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡

***ቁልፍ ቃላት፤*** አንብቦ መረዳት፣ የማጠቃለል ብልሃት

## 1. መግቢያ

በቋንቋ ትምህርት የማንበብ ክሂል በታሪካዊ ዳራው ረጅም ዕድሜና የበለጸገ መረጃ ያለው ቢሆንም ውስብስብ አዕምሯዊ ክንዋኔዎችን የያዘ በመሆኑ አንድ ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠት አልተቻለም፡፡ እንደሂደት ወይም የሂደቱ ውጤት አድርጎ ከማየት ባሻገር ማንበብ እስካሁን በግልጽ አልተበየነም (Brown, 2018; Duke & Pearson, 2009; Liu, 2010)፡፡ ለውስብስብነቱም ምክንያቶቹ ማንበብ ፍጥነት ያለው፣ መረዳትን የሚጠይቅ፣ መስተጋብራዊ፣ ብልሃታዊ፣ እንደማንበብ ዓላማው ተለዋዋጭ የሆነ፣ ገምጋሚነት ያለው፣ ሥነልሳናዊና የመማር ሂደቶችን የያዘ መሆኑ ናቸው (Grabe, 2009)። አንብቦ መረዳት ካለው ተፈጥሯዊ ውስብስብነት የተነሳም በቋንቋ ትምህርት መስክ እ.አ.አ ከ1975 ጀምሮ በጣም ጠቃሚ የምርምር ማዕከል ሆኖ ቀጥሏል (Al-Moman et al., 2014)፡፡

ክሂሉ ካለው ተፈጥሯዊ ባህርይ የተነሳም Khoshnevis (2015) እንደገለጹት አንብቦ በመረዳት ደካማ የሆኑ ተማሪዎች ስለሚያነቡት ጽሑፍ አወቃቀር ከጠንካራ ተማሪዎች ያነሰ ግንዛቤ አላቸው፡፡ ሐሳቦችን የማስታወስ ችግርም አለባቸው፡፡ የማንበብ ብልሃቶችን በመጠቀም ረገድም ውስንነት አለባቸው፡፡ ብዙ ተማሪዎችም ከጽሑፍ መልዕክት የመለየት ችግር አለባቸው፡፡ በዚህ የተነሳም በጥናት ጊዜ ችግሮች ይገጥሟቸዋል፡፡ በጽንሰሐሳቦችና በተማሪዎች አዕምሮ መካከል ዘፈቀዳዊ ግንኙነት ስለሌለ መረጃዎችን በቀላሉ ለማብላላት፣ ትውስታን ለማሳደግና የአዕምሮ ጫናን ለመቀነስ በአንባቢውና በጽሑፉ መካከል ትርጉም ያለው ግንኙነት መፈጠር አለበት፡፡ ይህም የተማሪዎችን መረጃ የማስታወስ ብቃት ይጨምራል፤ ችግር ፈቺ አንባቢም ያደርጋል፡፡

የብዙ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችግር ከመፍታት አንጻርም የማንበብ ብልሃቶችን ማስተማር አማራጭ መፍትሄ ነው፡፡ መምህራንም እነዚህን ብልሃቶች እንደአማራጭ ማስተማር ወይም ማሰልጠን ይኖርባቸዋል፡፡ ብልሃቶቹ፣ ተማሪዎች በማንበብ ሂደት ትጉህ እንዲሆኑና መረዳታቸው እንዲጨምር ይረዳሉ (Izquierdo & Jiménez, 2014)፡፡ ተገቢ የማንበብ ብልሃቶችን አለመጠቀምም አንባቢዎች ለማይጠቅሙ ዝርዝር ጉዳዮች ሁሉ ትኩረት እንዲሰጡ፣ የመረዳት ፍጥነታቸው እንዲቀንስና ጽሑፉን በተወሰነ የጊዜ ገደብ አንብበው እንዳይጨርሱ ያደርጋቸዋል፡፡ ከዋና ሐሳቦች ይልቅም በጽሑፉ ላዕላይ ክፍል እንዲያተኩሩ ያደርጋቸዋል፡፡

በመሆኑም ውስብስብ የሆነውን አንብቦ የመረዳት ተግባር በስኬት ለማከናወንም የተለያዩ ተቋሞችና ተመራማሪዎች (Al-Moman et al., 2014; Barber & Klauda, 2020; Lau & Chan, 2007; NRP, 2000; Talebi & Talebi, 2015) በጣም ጠቃሚና ወቅታዊ ያሏቸውን የማንበብ ብልሃቶች አስተዋውቀል፡፡ በስልጠና መልክ ከሚሰጡና ከውጤታማ አንብቦ የመረዳት ብልሃቶች መካከልም ማጠቃለል አንዱ ነው፡፡ ብልሃቱም ረጅም ታሪካዊ ዳራ ያለውና በአዕምሯዊ ሥነልቡናውያን የአዕምሮ መረጃ ማብላላት ንድፈሐሳብ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የማጠቃለል ብልሃት እንደሞዴል ዋና ዋና ሐሳቦችን፣ ጠቃሚ ዝርዝር ሐሳቦችንና አላስፈላጊ ሐሳቦችን መለየት፣ ዝርዝር ሐሳቦችን መጠቅለል፣ የተለያዩ አንቀጾችን ሐሳቦች ወደአንድ ማዋሐድ፣ የተጠቃለለውን ሐሳብ ማጥራት (*Polish*)፣ ለዚህም መረዳትን ርግጠኛ መሆን፣ ደጋግሞ ማንበብ፣ የሚሉ ጠቃሚ አላባዎችን የያዘ ነው (Hare & Borchardt, 1984)፡፡

ይህን ውስብስብነት ያለው ክሂል በመማር ማስተማር ሂደት በስኬት ማከናወንም አስቸጋሪ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ደረጃ በተለያዩ የትምህርት ርከኖች ክሂሉን በማስተማር ረገድ አተገባበራዊ ችግሮች መኖራቸውንም ጥናቶች ጠቁመዋል (Ministry of Education [MoE], 2018; Early Grade Reading Assessment [EGRA], 2010 & 2018)፡፡ አንብቦ የመረዳት ትምህርት የአተገባበርና ውጤት ችግሮች ያሉበት መሆኑንም የማስተዋል (2011) እና የታደሰ (2012) ጥናቶች ጠቁመዋል፡፡ ጥናቶቹ አንብቦ የመረዳት ችግርን ብቻ ሳይሆን ክሂሉ አስቸጋሪ ጉዳይ መሆኑንም አመላክተዋል፡፡

ማንበብን በመማር ማስተማር ክፍለጊዜያት ተማሪዎች እንዴት አንብበው እንደሚረዱ ለማስተማር አብዛኛዎቹ መምህራን በጣም ጥቂት ጊዜ ይሰጣሉ (Durkin, 1978)፡፡ ይህን ችግር ለመፍታትም የማንበብ ብልሃት ትምህርት አስፈላጊ ነው፡፡ በስልጠና ከሚሰጡ በጣም ጠቃሚና ወቅታዊ የማንበብ ብልሃቶች መካከልም የማጠቃለል ብልሃት አንዱ (Barber & Klauda, 2020; Lau & Chan, 2007; NRP, 2000; Talebi & Talebi, 2015)፡፡ የብልሃቱን አላባዎች በግልጽ ደረጃ በደረጃ ማስተማርም ተማሪዎችን አንብቦ በመረዳት ችሎታቸው እንደሚያሻሽላቸው ያረጋገጡ ጥናቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የBean and Steenwyk (1984); Braxton (2009); Chang et al, (2002); Graham and Hebert (2010) ጥናቶች ይጠቀሳሉ፡፡ የተለያዩ ጸሐፍት (Marzano et al., 2001; Wormeli, 2005) እንዲሁም ጥናቶች የብልሃቱን ውጤታማነት ያረጋገጡ ቢሆንም ብልሃቱ

ውጤታማ አለመሆኑን ያመላከቱ ጥናቶችም አሉ (Karbalaei & Rajyashree, 2010; Mehrdad et al., 2012; Hwang et al., 2019)፡፡

የትምህርትሚኒስቴር (2007ዓ.ም.) እና የአብክመ (2015ዓ.ም) የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ የተማሪ መጻሕፍት ሲታዩም ብልሃቱን ረቂቅ በሆነ በአዕምሮ መዋቅርመር (holistic) መልክ አካተዋል፡፡ ይህም ግልጽ ወይም መመሪያመር (step by step) የሆነው የመማር አቀራረብ በጥናት እንዲፈተሽ እድል ፈጥሯል፡፡

በአጠቃላይ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችግር መኖር፣ የቀደምት ጥናቶች ውጤት ልዩነትና የሥርዓተትምህርቱ አቀራረብ መዋቅር መር መሆን በዚህ ጥናት ቀጥተኛው አቀራረብ በሙከራ እንዲፈተሽ መነሻ ሆኗል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም ይህን ብልሃት በማንበብ ትምህርት ሂደት በግልጽ በማሠልጠን ተጽዕኖውን መመርመር ነበር፡፡

## 2. ክለሳ ድርሳን

### 2.1 የጥናቱ ንድፈሐሳባዊ መሠረት

አንብቦ መረዳት አንባቢ የቀደመዕውቀቱን ከአዲሱ የጽሑፍ ግብዓት ጋራ የሚያገናኝበት አዕምሯዊ ሂደት ነው፡፡ እንደሂደትም ከጽሑፍ ጋራ መስተጋብር በመፍጠር ቀጥተኛ፣ አመስጥሯዊና ሂሳዊ መረጃዎችን ለመለየትና ትርጉም ለማዋቀር ያስችላል (Antoni, 2010; Robinson & Good, 1987; Sabatini et al., 2013)፡፡ Al-Moman et al.(2014) እንደገለጹትም አንብቦ መረዳት፣ ትርጉም በመፍጠር ሂደት የችግር መፍቻ መንገድ ነው፡፡ ጥሩ አንባቢዎች፣ በቅድመ፣ በሂደትና በድኅረማንበብ ጊዜ የማንበብ ብልሃቶችን በንቃት ይጠቀማሉ፡፡ ከሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች መካከልም መረዳትን መቆጣጠር፣ በትብብር መማር፣ ማደራጃ ሠንጠረዥ፣ የታሪክ መዋቅር፣ ጥያቄ መመለስና ማፍለቅ፣ ማጠቃለል፣ ፈርጀብዙ ብልሃቶች ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡

ከላይ ከቀረቡት የማንበብ ብልሃቶች መካከል የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው በማጠቃለል ማንበብ ነው፡፡ ይህ ብልሃት ጽሑፎችን አብላልቶ ለመረዳት የሚያስችልና ለተማሪዎችም ራሱን ችሎ በስልጠና መልክ ሊሰጥ የሚችል ነው፡፡ ታሪካዊ ዳራውም ከHarris (1952) ሥራ የሚነሳ ሲሆን እ.አ.አ. ከ1978 ጀምሮም በዘመናዊ መልክ እየተጠና መጥቷል፡፡ በዚህ መልክ እንዲጠና

ምክንያት የሆነው ደግሞ መመሪያመር አቀራረብ (rule-governed approach) የሆነው የKintsch and Van Dijk (1978) የማጠቃለል ብልሃት ሞዴል ነው፡፡ ሞዴሉ ለጽሑፍ ውቅርና ለማጠቃለል እውቅና መስጠቱ ለመስኩ ጥናቶች መስፋፋት ምክንያት ሆኗል (Karbalaei & Rajyashree, 2010)፡፡ ሞዴሉን Hare and Borchardt (1984)ና ሌሎችም የተለያዩ መመሪያዎችን በመጨመር አሻሽለውታል፡፡ Karbalaei and Rajyashree(2010) እንደገለጹትም በሞዴሉ አንባቢያን እንዴት እንደሚያጠቃልሉ የሚያግዙ አስፈላጊ አላባዎችን ይማራሉ፤ መመሪያዎችንም በማመሳከሪያነት (cheklist) ይጠቀማሉ፡፡ Duke and Pearson (2009); Marzano et al. (2001) እና Wormeli (2005) በበኩላቸው፣ ሞዴሉ ደረጃ በደረጃ ሂደቶችን የሚከተልና መረጃዎችን በንቃት ለማብላላት የሚያስችል ቀደምትነት ያለው ነው፡፡ ቀጥተኛና መደበኛ የማጠቃለል መርሆችን የያዘ በመሆኑም ተማሪዎችን በከፍተኛ ሁኔታ ስኬታማ ያደርጋል፡፡

የብልሃቱ መነሻ አዕምሯዊ የመረጃ ማብላላት ንድፈሐሳብ ነው፡፡ ንድፈሐሳቡ Alexander and Fox (2004) እንደገለጹት እ.አ.አ. ከ1976-1985 ባለው ዘመን የተዋወቀና የበላይነት የያዘ ነበር፡፡ ከባሕርያውያን አተያይ በተቃራኒም ለአንባቢ ትኩረት የሰጠ ነው፡፡ በንድፈሐሳቡ አተያይ አንብቦ የመረዳት ሂደቱ ላይታች (top-down) ሲሆን ማንበብ የሚጀምረውም ከአንባቢ የቀደመ መረጃ ነው (Snowling & Hulme, 2005)፡፡ እንደ Pardede (2008) እና Alexander and Fox አገላለጽም፣ ዳራዊ ዕውቀትና የአዕምሮ መዋቅር ንድፈሐሳቦችም የዘመኑ ትሩፋት ናቸው፡፡ ማንበብም የአንባቢና የጽሑፉ ንቁ ተራክቦ ሲሆን ንቁ አዕምሯዊ ሂደትን ይከተላል፤ ትርጉም ለመፍጠርም ዳራዊ ዕውቀት ቁልፍ ሚና አለው፡፡ በማንበብ ጊዜም የአንባቢውንና ጽሑፉን መስተጋብር መምራትና መቆጣጠር ከመምህራን ይጠበቃል፤ ተማሪዎች ማስታወሻ እንዲይዙና መረጃዎችን እንዲያጠቃልሉ ማድረግም ዋና ተግባራቸው ነው፡፡

Savolainen (2018) እና Weibell (2011) እንደገለጹት አዕምሯዊ የመረጃ ማብላላት ንድፈሐሳብ፣ ልዕለአዕምሯዊና አዕምሯዊ መረጃ የማብላላት ቁልፍ አላባዎችን ይይዛል፡፡ እነዚህም Schunk (1996) እንደገለጹት ተማሪዎች በንቃት መረጃ እንዲፈልጉና መረጃ እንዲያብላሉ ያግዟቸዋል፡፡ መረጃ ለማብላላት የሚረዱ ብልሃቶችን ለአንባቢያን ማሰልጠን ላይ ያተኮሩ ጥናቶች ሰፊ ናቸው (Bean & Steenwyk, 1984; Brown, 2018; Brown & Day, 1983)፡፡ Wegner et al. (2013) እንደገለጹትም ንቁ አዕምሯዊ መረጃ ማብላላት የሚፈጥሩ የመማር ብልሃቶች (ለምሳሌ፦ ማስታወሻ መያዝና ማጠቃለል) በተማሪዎች ተነሳሶት፣ ትኩረት፣ መረጃ መረጣ፣ ማብላላትና

**ማደራጀት ላይ ተጽዕኖ አላቸው፡፡ ተመራማሪዎችም ብልሃቶችን በግልጽ በማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ አሻሽለዋል፡፡ እነዚህ ስኬቶችም አዕምሯዊ መረጃ የማብላላት ሞዴሎች ለማንበብ ሂደት ማሕቀፍ ሆነው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ጥንካሬና ድጋፍ ሰጥተዋል፡፡**

**በንድፈሐሳቡ አተያይ፣ የማጠቃለል ብልሃት ጽሑፍን አንብቦ በመረዳት ሂደት መሠረታዊ ነው፡፡ ከአንደኛ ደረጃ ኹለተኛው ርከን ጀምሮም ተማሪዎች ሊማሩት ይችላሉ** (Gelati et al., 2014):: **ጽሑፍን በጥልቀት ለመረዳትም ያስችላል** (Cho, 2012; Marzano et al., 2001; Pečjaka & Pirc, 2018; Westby et al. 2010)፡፡ **ብልሃቱ ከሚነበበው ጽሑፍ ጠቃሚውን ሐሳብ ለመለየት፣ አላስፈላጊውን ለማስወገድ፣ የቀረበውን ጽሑፍ ማዕከላዊ ሐሳብ በጽሑፍ በአጭር ጨምቆ ለማዋቀርና መልሶ ለመፍጠር ያስችላል፡፡ ብልሃቱ የመሰረዝ፣ የመተካት፣ የመለየትና ዋናውን ጽሑፍ ጠብቆ አሳጥሮ የመጻፍ** (deleting, substituting and keeping information) **ሂደት ነው፡፡ ብልሃቱ ከቀረበ ጽሑፍ እያነበቡ መጻፍንና እየጻፉ ማንበብን አቀናጅቶ የያዘ ነው፡፡ ጽንሰሐሳባዊ ማሕቀፍ በመሆንም የአንባቢን የረጅም ጊዜ ትውስታ፣ መልሶ መጠቀምና መረዳት ከፍ ያደርጋል** (Chiu, 2015; Corder-Ponce, 2000; Graham and Hebert, 2010; Karbalaei & Rajyashree, 2010; NRP, 2000; Wormeli,2005)፡፡

Al-Momani et al. (2014); Barreiro (2019); Marzano et al. (2001) **እና** NRP (2000) **እንደገለጹትም ብልሃቱ በማንበብ ወይም በድኅረማንበብ ጊዜ ተግባራዊ በመሆን አንባቢያን ትጉህ** (engagement) **እንዲሆኑ፣ ደጋግመው እንዲያነቡና በጥልቀት እንዲረዱ ያበረታታል፡፡** Graham and Hebert (2010) **እንደገለጹትም ብልሃቱ አንብቦ መረዳትን እንደሚያጎለብት ሰፊ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ነገርግን ብልሃቱን በማስተማር ረገድ የተሻለው በግልጽ** (explisit) **ወይስ ተፈጥሯዊ** (implicit) **በሆነው አቀራረብ ማቅረብ? የሚለው ጉዳይ ወጥ ድምዳሜ አልተደረሰበትም፡፡ ለዚህም የ**Al-Darayseh (2014); Maxwell (2014); Taki (2017) **እና** Tiruneh (2014) **ጥናቶች አስረጂዎች ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ግን** Al-Momani et al. **እና** Barreiro "**በተለይ አንብቦ የመረዳት ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የብልሃቱን መመሪያዎች በግልጽ አቀራረብ ከመማር ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡**" **በማለታቸው ይህ አቀራረብ ተመርጧል፡፡**

## 2.2 የማጠቃለል ብልሃት አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተጽዕኖ

የማጠቃለል ብልሃት አንብቦ ከመረዳት ጋራ ጥብቅ ግንኙነት አለው፡፡ በመሆኑም አንባቢያን በማንበብ ሂደት ንቁ እንዲሆኑ፣ ጊዜ እንዲወስዱ፣ መረጃ እንዲያብላሉ፣ ልዕለአዕምሯዊ ቁጥጥር እንዲያደርጉ፣ ሌሎች አዕምሯዊ ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ ያደርጋቸዋል (Braxton, 2009; Brown & Day, 1983; Brown et al., 1983; Khoshnevis & Parvinnejad, 2015; Özdemir, 2018)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች በጽሑፍ ውስጥ ያሉ ጽንሰሐሳቦችን ትስስር እንዲገነቡ፣ ጽንሰሐሳቦችን ከቀደመዕውቀታቸው ጋራ እንዲያገናኙና ትኩረት እንዲሰጡ በማድረግ መረዳታቸውን፣ መረጃዎችን በረጅም ጊዜ የማስታወስና መልሶ የመጠቀም ብቃታቸውን ያሻሽላል (Bean & Steenwyk,1984; Braxton, 2009; Brown & Day, 1983; Chang et al., 2002 ; Garner, 1985; Karbalaei & Rajyashree, 2010)፡፡

የማጠቃለል ብልሃት አንብቦ መረዳትን ከማሳደግ አንጻር ጉልህ ድርሻ መኖሩ ቢገለጽም በጉዳዩ ላይ የተደረጉ ምርምሮች በሥነልሳናውያን የተገለሉ ነበሩ፤ ብልሃቱም ችላ ተብሎ ቆይቷል (Hutchins, 1987)፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የሥነትምህርት ተመራማሪዎችና የአዕምሯዊ ሳይንቲስቶች በትውስታና ክምችት (recall and remembrance) ላይ ስላለው ሚና እየመረመሩት ነው፡፡ የሰውሠራሽ አስተውሎት (artificial intelligence) ተመራማሪዎችም መስኩን እየመረመሩት ይገኛሉ፡፡ በመስኩ የተከናወኑ ፍትነትመሰል ጥናቶች ውጤታማነትም የብልሃቱ ሞዴሎች መጠናታቸው እንዲቀጥል አድርጓል፡፡ የብልሃቱን ውጤታማነት ያመላከቱ ቀደምት ጥናቶች ቢኖሩም ሁሉም ግን አንድ ወጥ ድምዳሜ ላይ አልደረሱም፡፡ ለምሳሌ፣ የAghaie and Zhang , (2012); Bahrami and Rahimy (2022); Barreiro (2019); Chang et al. (2002); Graham and Hebert (2010) እና Nelson et al. (1992) ጥናቶች ብልሃቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማሻሻሉን አሳይተዋል፡፡ በአንጻሩ ብልሃቱ አንብቦ በመረዳት ላይ ተጽዕኖ የለውም፤ ከአፍመፍቻና ከኹለተኛ ቋንቋ እንዲሁም ከጾታ አንጻርም የውጤት ልዩነቶች መኖራቸውን ያመላቱ ጥናቶች አሉ (Braxton, 2009; Hwang et al., 2019; Karbalaei & Rajyashree, 2010; Mehrdad et al., 2012; Tobing, 2013; Zhang et al., 2008)፡፡ ይህም ጉዳዩ በተለያዩ የምርምር ንድፎች፣ በአፍመፍቻና በኹለተኛ ቋንቋዎች መጠናቱ እንዲቀጥል በር ከፍቷል፡፡ ወቅታዊነቱም ትኩረትን ስቧል፡፡ ለዚህም የSolikhah and Sari (2022) እና የBahrami and Rahimy (2022) ጥናቶች አስረጂዎች ናቸው፡፡

በአፅምሯዊ የመረጃ ማብላላት ንድፈሐሳብ ላይ የተመሠረተው ይህ ጥናትም፤ የማንበብ ብልሃቱን በቀጥታ የማስተማር ሂደትን ተከትሏል፤ የክፍል ውስጥ የብልሃት ልምምድ ሂደቱም ልሥራ፣ እንሥራ፣ ሥሩ የሚለውን የማኅበረግንባታውያን ንድፈሐሳብ ሞዴል ተከትሏል፡፡

## 3. ጽንሰሐሳባዊ ማሕቀፍ

በጥናቱ ዳራና መነሻ ችግር ከቀረቡት ድርሳናት ለመረዳት እንደተቻለው የጥናቱ ተላውጦዎች መንስዔያዊ ግንኙነት ተሰተውሎባቸዋል፤ በዚህ ጥናት የተፈተሸውም በምስል 1 የተመለከተው ጽንሰሐሳባዊ ሞዴል ነው፤

**ምስል 1**

*የጥናቱ ጽንሰሐሳባዊ ሞዴል*




በሞዴሉ እንደተስተዋለው የጥናቱ መነሻ የማጠቃለል ብልሃትን በማንበብ ትምህርት ላይ በማስተማር ወይም በማሰልጠን መጠቀም ነው፡፡ ይህ ሂደትም በቀጥታ በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ጥናቱ በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት በማጠቃለል ብልሃት ማንበብን መማር አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ መርምሯል፡፡ በዚሁ መሠረት የተፈተሹ መላምቶችም የሚከተሉ ናቸው፤

H1፡ የማጠቃለል ብልሃት አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ አለው፡፡

H0: የማጠቃለል ብልሃት አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ የለውም፡፡

## 4. የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት ፍትነትመሰል (Quasi-expermental) የምርምር ንድፍን የተከተለ ነው፡፡ ለዚህም ቅድመ-ድኅረፈተና ባለቁጥጥር ቡድን ንድፍ (two group pre-post test design) ተተግብሯል፡፡

## 4.1 ተሳታፊዎች

በጎንደር ከተማ አስተዳደር፣ የአጼበካፋ አጠቃላይ አንደኛ ደረጃ ትምህርትቤት የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ናቸው። ትምህርትቤቱ የሙከራ ጥናቱ ከተካሄደበት ትምህርትቤት ርቀት ካላቸው ፈቃደኛ ተምህርትቤቶች በቀላል ዕጣ የተመረጠ ነው። በትምህርትቤቱም በ2015 ዓ.ም. ሦስት የሰባተኛ ክፍል (ሴክሽን) ተማሪዎች ነበሩ። እነዚህ ክፍሎች በአንድ የአማርኛ መምህር ሲማሩ ነበር። ከእነዚህም ለምርምር ሥራው ኹለቱ ($7^1$ና $7^3$) በተራ ዕጣ ንሞና ተመርጠው ተማሪዎቹ የይሁንታ ስምምነት እንዲሞሉ ተደርጓል። ከእነዚህም ቅድመትምህርት መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ መደበኛውን ትምህርት ለመማር በተመደቡባቸው ክፍሎች በተራ ቡድናዊ ዕጣ ንሞና ዘዴ $7^1$ ለሙከራና $7^3$ ለቁጥጥር ሆነው ተመድበዋል። በጥናቱም በሙከራ ቡድኑ 51 (29 ሴት፣ 22 ወንድ)፣ በቁጥጥር ቡድኑ 51 (32 ሴት፣19 ወንድ) ተማሪዎች ተሳትፈዋል።

በጥናቱ የተፈተሹት ተላውጦዎች ከአራተኛ ክፍል በላይ ባሉ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ሊተገበሩ የሚችሉ ናቸው። ነገርግን በመካከለኛው የክፍል ደረጃ በማጠቃለል ብልሃት ማንበብ የበለጠ አዋጭ መሆኑን ጥናቶች (Bean and Steenwyk, 1984; Butler et al,2010) በመጠቆማቸው የሰባተኛ ክፍል ተመርጧል። ከዚህም በተጨማሪ የክፍል ደረጃው ክልልአቀፍ ፈተና ለመፈተን የሚዘጋጁበትና ወደኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ርከን የሚሸጋገሩበት ዋዜማ በመሆኑ ብቁ ሆነው እንዲሸጋገሩ ማስፈለጉ ተመራጭ አድርጎታል። አንብቦ መረዳት የኹለተኛ ደረጃ ትምህርት መሠረት በመሆኑ በዋናነት በላይኛው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ርከን ጠቃሚ ነው (በButler et al., 2010 ዋቢ. የተደረጉት Sweet and Snow, 2003)።

## 4.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ

በዚህ ጥናት የማጠቃለል ብልሃት ተተግባሪ ተላውጦ ነው፤ በመሆኑም የሚለካ አይደለም። የመተግበሩ ምክንያትም የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችግርና የቀደምት ጥናቶች የውጤት ልዩነቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በመሆኑም የጥናቱን መረጃ ለመሰብሰብ የዋሉት ትይዩ አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች ናቸው። እያንዳንዱ ፈተናም ቀጥተኛ፣ እንድምታዊና ሂሳዊ መረዳትን የሚጠይቁ 36 በባለአራት አማራጭ ስልት የቀረቡ ጥያቄዎችን ይዟል። እያንዳንዳቸውን ለመሥራትም 1፡00 ተሰጥቷል። ፈተናዎቹም በHashim (2014)ና Indillah (2020) አንብቦ

መረዳት ፈተና መወሰኛ ሞዴሎችና በክፍል ደረጃው የሚጠበቀውን አንብቦ የመረዳት ንድፈሐሳባዊ ባሕርያት (theoretical construct) መሠረት በማድረግ በአጥኚው ተዘጋጅተዋል፡፡ ፈተናዎቹ አስረጂ ምንባቦች ላይ ተመሥርተዋል፡፡ አጥኚው ካቀርባቸው 11 መረጃሰጪ ምንባቦች አልበርት አይንስታይን(1)ና ፑሽኪን(2) የተሰኙት በክፍል ደረጃው የኹለት ትምህርትቤት መምህራን የተገቢነት ግምገማ ተመርጠዋል፡፡ ፈተናዎቹ በሙከራ ጥናት ወቅት ቅድመትምህርት በ109 ተሳታፊዎች የፈተና አንድና ኹለት ትይዩነት በክምባኽ አልፋ (*r.* = .714) ሆኗል፡፡ አስተማማኝነታቸው በእኩል ክፋይ ስልት በሁሉም ተሳታፊዎች (109) በፈተና አንድ *r.* = .782፣ ፈተና ኹለት ደግሞ *r.* = .741 ሆኗል፡፡ የይዘት ትክክለኛነታቸው እኩልዮሽ (ሬሾ) በLawshe (1975) ቀመር ተሰልቷል፤ ውጤቱም (.99) ሆኗል፡፡ አስተማማኝነታቸውና ትክክለኛነታቸው በሙከራ ከተፈተሸ በኋላም አንደኛው (አልበርት አይንስታይን) ለቅድመ ሌላኛው (ፑሽኪን) ለድኅረትምህርት ፈተናነት ውለዋል፡፡ በዋናው ጥናት ወቅት የቅድመትምህርት ፈተናው አስተማማኝነት በሙሉና በጎደሎ ተመድበው የተገኘው አስተማማኝነት *r.*= .722፤ የድኅረትምህርት ፈተናው ደግሞ *r.*=.815 ሆኗል፡፡ በቅድመትምህርት (102) በተገኘው መረጃ የጥያቄዎች የባሕርይ ትክክለኛነት (construct validity) እያንዳንዱ ጥያቄ ከድምሩ ጋራ ያለው ተዛምዶ ተሰልቶ በመካከላቸው አዎንታዊ ተዛምዶ አሳይተዋል፡፡

### 4.4 የአጠናን ሂደትና አተገባበር

#### 4.4.1 የማስተማሪያ መሣሪያ አዘገጃጀት

በዚህ ጥናት የማጠቃለል ብልሃትን አንብቦ በመረዳት ትምህርት ለመተግበር የሚያስችል የማስተማሪያ መሣሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ መሣሪያው የቀጥታ/ግልጽ የብልሃት ትምህርት፣ የሞዴል፣ የቡድንና የግል የልምምድ ደረጃዎችን የያዘ ነው፡፡ ይኸውም በEl-Koumy (2016) ዋቢ የተደረጉት Duke (2001) ያዘጋጁትን የማንበብ ብልሃት ማስተማሪያ ሞዴል የተከተለ ነው፡፡ ግልጽ የብልሃት ትምህርት ደረጃው በኹለት ክፍለጊዜ በንድፈሐሳብ ደረጃ ስለማጠቃለል የማንበብ ብልሃት ምንነት፣ አስፈላጊነት፣ መመሪያዎች፣ መቼና እንዴት እንደሚጠቀሙበት እንዲሁም በአተገባበር ደረጃ ዝርዝር ስልቶች (እንደጽሑፍ አደረጃጀቱ መረጃ ለመለየት የሚያስችሉ ጥያቄዎች) ምን እንደሚመስሉ ይዟል፡፡ ሞዴል ትምህርቱ በኹለት፣ የቡድን ትምህርቱ በአራትና የግል ልምምዱ በአራት ምንባቦች በድምሩ 10 የሥርዓተትምህርቱ

ምንባቦች ከነመልመጃቸው ተዘጋጅተዋል፡፡ ይህን ትግበራ ለመደገፍ ደግሞ የማጠቃለል ብልሃቱ መመሪያዎች ቅጽ (Rule sheet)፣ የመምህርና የተማሪ መጸብረቂያ ቅጾች ተዘጋጅተዋል፡፡

### 4.4.2 የትግበራ ሂደት

የዚህ ጥናት ሂደት፣ በቅድሚያ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችና የማስተማሪያ መሣሪያው በአጥኚው ተመርጠዋል፤ ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህ መሣሪያዎችም በቅድሚያ በባለሙያዎች ግምገማዊ አስተያየት እንዲሰጥባቸው ተደርጓል፡፡ ተደጋግመውም ተከልሰዋል፡፡ ቀጥሎም ከጥናቱ ተሳታፊዎች ቅድመትምህርት መረጃዎች ተሰብስበው የ12 ሳምንት ትምህርት ከተሰጠ በኋላ ድኅረትምህርት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በዚህም የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ፍተሻ ተደርጓል፡፡ የሙከራ ትምህርቱም በአጥኚው የግንዛቤና የአተገባበር ስልጠና በተሰጣት መምህርት በታቀደለት ጊዜ ቀርቧል፡፡

ለመረጃው ውስጣዊ ትክክለኛነት ሲባልም ቅድመትምህርት ፈተናዎችን ማስታወሻ ሳይዙ እንዲፈተኑ ተደርጎ መረጃዎቹ ተሰብስበዋል፡፡ ፈተናዎቹም ሙሉ በሙሉ ተሰብስበዋል፡፡ በክፍል ውስጥ ለልምምድ የዋሉ የማጠቃለያ መመሪያዎችና ቅጾች በየክፍለጊዜው መጨረሻ ተሰብስበዋል፡፡ ኹለቱም ቡድኖች ተመሳሳይ አንብቦ የመረዳት ፈተና፣ የፈተናና የትምህርት ጊዜና የፈተና እርማት ሂደት እንዲሁም ትምህርቱን በአንድ መምህርት እንዲማሩ ሆነዋል፡፡ የሙከራው ቡድን ለቁጥጥሩ መረጃዎችን እንዳይሰጡ ስለምርምሩ ዓላማ የማስገንዘብ ሥራ ተሠርቷል፡፡ ለቁጥጥር ቡድኑም ከፈተና በኋላ የሙከራ ቡድኑ በተማረበት ብልሃት ትምህርቱ እንደሚካካስለት መተማመን ላይ ተደርሶ ጥናቱ ተከናውኗል፡፡

### 4.4.3 የመረጃ ትንተና

#### 4.4.3.1 የቅድመሁኔታ ትንተና

ይህ ጥናት ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ ከተካሄደ ጥናት በከፊል የተወሰደ ነው፡፡ በጥናቱ የመረጃ ትንተናም አበር ተኮር መዋቅራዊ የትንተና ሞዴል (spss v.20-CB-SEM-AMOS (Covariance-based structural equation modeling) ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ለዚህም በጥናቱ ውጤት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ፆታ፣ ዕድሜና ችሎታ እንዲሁም የመረጃዎች ቀጥተኛ ግንኙነት፣ የመረጃዎች የስርጭት ወጥነትና የልይይት ስሕተት አንድነት በቅድመሁኔታ ፍተሻዎች

ታይተዋል። በቅድመትምህርት በኹለቱ ክፍል ተማሪዎች መካከል የፆታ ምጥጥኖሹ በካይ ካሬ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ($X^2$ = 3.922, p=.048) ሆኗል። ይህም በክፍሎቹ መካከል ልዩነት መኖሩን የሚያሳይ በመሆኑ ፆታ በአበር ተላውጦነት ቁጥጥር ተደርጎበታል። የተሳታፊዎች በየክፍሉ በዕድሜ መመጣጠን በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት $t$(100)= .314; $P$=.754 ሆኗል። አጠቃላይ ዕድሜያቸውም ተቀራራቢ ነው። አማካይ ዕድሜያቸውም በ7[1] 13.88 ሲሆን በ7[3] ደግሞ 13.96 ነው። በመሆኑም ዕድሜ በድኅረትምህርት በአበር ተላውጦነት ጥቅም ላይ አልዋለም።

ከዚህም በተጨማሪ አንብቦ የመረዳት መረጃዎች ለትክክለኛው መልስ "1"፣ ለተሳሳተው መልስ "0" ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ሞዴሉ የሚፈልገው መጠናዊ ጥገኛ ተላውጦ በመሆኑ በመደመር ወደመጠናዊ መረጃ ተቀይረዋል። ይህ የተሳታፊዎች አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤትና የልይይት ስሕተት አንድነትም በነጻ ናሙና ቲ-ቴስትና በለቨን ቴስት ተፈትሿል። በቅድመትምህርት የተገኘው ውጤት በቅደምተከተል $t$(100)= .267, $p$=.790፤ $F$(1, 100)= 3.720, $p$=.057 ሆኗል። የኹለቱ ክፍሎች ድኅረትምህርት የልይይት ስሕተት አንድነትም $F$(1, 100)=.419, $p$=.519 ሆኗል። የመረጃዎቹ የስርጭት ወጥነትም በቅድመትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተናው በኮልሞግሮቭ ተፈትሾ የተገኘው ውጤት በክፍል 7[1] እና 7[3] በተከታታይ $P$= .193 እና $P$= .200 ሆኗል። በድኅረትምህርት ፈተናው የተገኘው ውጤት ደግሞ በየቡድኑ $P$= .200 ሆኗል። የተላውጦ ቀጥተኛ ግንኙነትን በተመለከተም የሙከራ ቡድኑ (7[1]) ቅድመትምህርት አንብቦ መረዳት ከድኅረትምህርት አንብቦ መረዳት ጋራ የቀጥተኛነት (Linearity) ጉልህነቱ $p$= .001 ሲሆን ከቀጥተኛነት ያለ ልይይት (Deviation from Linearity) $p$= .437 ሆኗል። የቁጥጥር ቡድኑ (7[3]) ቅድመትምህርት አንብቦ መረዳት ከድኅረትምህርት አንብቦ መረዳት ጋራ የቀጥተኛነት ጉልህነቱ $p$= .001 ሲሆን ከቀጥተኛነቱ ያለ ልይይት ደግሞ $p$= .051 ሆኗል።

የትንተና ሞዴሉን ለመጠቀም ከላይ ከተፈተሹ ቅድመሁኔታዎች በተጨማሪ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ የመማር ብልሃቶች መንትያ ምድባዊ ተላውጦ (dummy variable) ሆነዋል። ይሄውም የሙከራ ቡድኑ (7[1]) የተማረበት ብልሃት 1 እና የቁጥጥር ቡድኑ (7[3]) የተማረበት ብልሃት 0 (dummry coded) ሆነው ተመድበዋል። ትንተናውም ትክክል የመሆን እድልን ከፍ በሚያደርገው ቴክኒክ (maximum likely hood) ተሠርቷል። የትንተና ሞዴሉ በባሕርይው

**የመተማመኛ ደረጃ ውጤት በቀጥታ ስለማያሳይ ይህንን ለማግኘት የመዋቅራዊ ትንተና ሞዴሉ አካል የሆነው ናሙና አካይ** (bootstrap) **ምልክት እንዲነቃ ሆኗል፡፡ ለዚህም የትንተና "ማሽኑ" በታቀደለት ልክ 5,000 ናሙና ተጨምሮለታል፡፡ መረጃውም ለመላምታዊ ሞዴሉ ያለው ስምሙነት** (model fit) **ተቀባይነት ያለው ሆኗል፡፡ ውጤቱም በምስሉ ላይ ሠፍሯል፡፡ በአጠቃላይ የትንተና ሞዴሉን ለመጠቀምም ቅድመሁኔታዎች ተሟልተዋል፡፡**

### 4.4.3.2 የመላምት ፍተሻ

**የጥናቱን መላምት በመፈተሽ ረገድም በመረጃ ትንተናው ሂደት ፆታ፣ ቅድመትምህርት አንብቦ መረዳት፣ አጠቃሎመጻፍና የማንበብ ተነሳሶት አንብቦ በመረዳት ላይ በተከታታይ በ95% ናሙና አካይ የመተማመኛ ደረጃ** (*B* = -2.066, *S.E.* =.804, *P*=.010; *B* =.413, *S.E.* =.082, *P*=.001; *B* =.252, *S.E.* =.150, *P*=.093; *B* =2.801, *S.E.* =.786, *P*=.001) **ተጽዕኖ ያሳደሩ በመሆኑ በአበር ተላውጦነት ቁጥጥር ተደርጎባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ እንደተመለከተው፣ ድኅረትምህርት የማንበብ ተነሳሶትና አጠቃሎ መጻፍ በትንተና ሞዴሉ የነበራቸው ኢቀጥተኛ የተጽዕኖ ድርሻ ቁጥጥር ተደርጎባቸው የተሠራ ነው፡፡**

*የማጠቃለል ብልሃት አንብቦ በመረዳት ላይ ያለው ተጽዕኖ የተስተካከለ (adjusted) ምጣኔ*

| መላምት | ተጋርቶሽ ($R^2$) | ድኅረት (*B*) ቀጥተኛ | መደበኛ ስሕተት (S.E) | 95%CI LL | 95%CI UL | *P*(ባለ2 ጫፍ) | η2 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| H1. ማጠ.ብ. → አንብመ.ች. | .48 | 2.72 | .826 | 1.078 | 4.292 | .001 | .25 |


*ማጠ.ብ.= የማጠቃለል ብልሃት* =*CR(t) >1.96= p<.05*
*አንብመ.ች=የአንብቦ መረዳት ችሎታ* =*for* $R^2$, *p<.05*

**የጥናቱን መላምቶች በመፈተሽ ረገድ የመዋቅራዊ ትንተና ሞዴሉ እንዳሳየውም የማጠቃለል ብልሃት አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ ጉልህ አዎንታዊ ቀጥተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ በኹለቱ ቡድኖች መካከል የታየው የአማካይ ውጤት ልዩነትም በ95% ናሙና አካይ የመተማመኛ ደረጃ** ($R^2$=.48, *B* = 2.72, *S.E*=.826, *P*= .001, *CI* [1.078, 4.292], *η2*= .25) **ሆኗል፡፡ ብልሃቱ አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ ያሳደረው የተጋርቶሽ ምጣኔም (48%)፣ የተጽዕኖ ጥንካሬው ወይም ጉልህነቱ ደግሞ በኮህን የፍትነትመሰል ጥናት የመቁረጫ ነጥብ መሠረት** η2= .25 **(ከፍተኛ)**

ሆኗል፡፡ በመሆኑም አልቦ መላምቱ ውድቅ ሆኖ አማራጭ መላምቱ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ በመዋቅራዊ ሞዴሉ የተገኘው ውጤትም ቀጥሎ በቀረበው ምስል ተመልክቷል፡፡

**ምስል 2**

*የጥናቱ ንድፈሐሳባዊ የትንተና ሞዴል ኢመደበኛ ምጣኔ*




በምስሉ እንደተስተዋለው በጥናቱ በምድባዊ (dummy) ተላውጦ ሆነው "ኮድ" የተደረጉ አንድ ሙከራ (ኮድ"1")ና አንድ የቁጥጥር (ኮድ "0") ቡድን በቀዳሚው ሳጥን ተመልክተዋል፡፡ በዚሁ ሳጥን አናት ላይ የተመለከተው .485 (48%) ደግሞ ብልሃቱ አንብቦ በመረዳ ችሎታ ላይ ያሳደረው የተጋርቶሽ ዋጋ ( $R^2$) ነው፡፡ በኹለቱ ሳጥኖች መካከል የሰፈረው ውጤት (2.72) ደግሞ በቡድኖች መካከል የተገኘው አማካይ ውጤት ልዩነት ነው፡፡ የውጤቱ አዎንታዊ መሆንም የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥሩ ውጤት ከፍ ያለ መሆኑን አማላካች ነው፡፡ በኹለተኛው ሳጥን አናት ላይ በክቡ ውስጥ ተስተዋለው ውጤት (15.7) ደግሞ ኢመደበኛ የስህተት (error term) መጠን ነው፡፡

በአጠቃላይ የጥናቱ ውጤት ቅድመትምህርት መረጃዎች፣ ፆታና ኢቀጥተኛ ተጽዕኖ የነበራቸው ተላውጦዎች ቁጥጥር ተደርጎባቸው የተገኘ ነው፡፡ ውጤቱም በማጠቃለል ብልሃት አንብቦ መረዳትን የተማረው የሙከራ ቡድኑ በመደበኛው ብልሃት ማንበብን ከተማረው የቁጥጥር ቡድኑ በ2.72 አማካይ ውጤት ከፍ በማለት (success rate) ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፡፡

## 5. የውጤት ማብራሪያ

ጥጥናቱ በማጠቃለል ብልሃት ማንበብን መማር በተማሪዎች አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ የመረመረ ነበር፡፡ የመረጃ ትንተናው እንዳመለከተውም ብልሃቱ አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ ጉልህ አዎንታዊ ቀጥተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ በሙከራና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል የታየው የአማካይ ውጤት ልዩነትም በ95% ናሙና አካይ የመተማመኛ ደረጃ ($R^2$=.48, *B* = 2.72, *S.E*=.826, *P*= .001, *BCI*[1.078, 4.292], $\eta 2$=.25) ሆኗል፡፡ ይህ ልዩነት የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በማጠቃለል ብልሃት ማንበብን በመማራቸው የመጣ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ Collier (2020, p. 241) እንደገለጹትም በሞዴሉ በነጻና በጥገኛ ተላውጦዎች የግንኙነት መስመር ላይ የሚገኘው ምጣኔ አዎንታዊ መሆኑ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የተማሩበት ብልሃት የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ከተማሩበት መደበኛው ሥርዓተትምህርት ብልሃት ብልሃት የተሻለ ተጽዕኖ የፈጠረ መሆኑን አመላካች ነው፡፡

ይህ ውጤት ምንም እንኳ የትንተና ስልታቸው የተለያየ ቢሆንም ብልሃቱ በአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩን ካረጋገጡት ከNelson et al (1992) ንጥልና ከChang et al (2002) ፍትነትመሰል ጥናቶች ውጤት ጋራ ተመሳሳይ ነው፡፡ በNelson et al ጥናት የ(Hare and Borchardt (1984) የማጠቃለል ሞዴል በቀጥተኛ ገለጻ፣ ሞዴልና መርልምምድ በቡድን፣ በግልና በክትትል ቀርቧል፡፡ በChang et al ጥናት ደግሞ ጽንሰሐሳባዊ የማጠቃለል ብልሃትን ለሰባት ሳምንት በመደበኛው ክፍል በአፍፊት ተማሪዎች ላይ ተተግብሯል፡፡

የተገኘው ውጤት ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ላሉ የተለያዩ የትምህርት ርከን ተማሪዎች ብልሃቱን በግልጽ አስተምረው አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው መሻሻሉን ካረጋገጡ ከAghaie and Zhang (2012); Bahrami and Rahimy (2022); Barreiro (2019); Brown and Day (1983); Cordero-Ponce (2000); Khoshsima and Tiyar (2014); Lau and Chan (2007); Li et al (2022) እና Taylor and Beach (1984) ፍትነትመሰል ጥናቶች ጋራም ተደጋጋፊነት አለው፡፡ ብልሃቱ የተማሪዎችን

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማሻሻሉን ካረጋገጠው የStevens et al (2019) ክልስ ጥናት ጋራም ትይዩ ነው፡፡ ውጤቱ በትምህርት ታሪክ ውስጥ ማጠቃለል በጣም ውጤታማ ከሚባሉት ብልሃቶች አንዱ ነው፤ ያሉ የBogoya (2011); Marzano et al. (2001)እና Wormeli (2019)ን ሐሳብም ደግፏል፡፡

በአንጻሩ የዚህ ጥናት ውጤት ፍትነትመሰል ንድፍን ተከትለው ብልሃቱን ውጤታማ አይደለም ካሉት ከKarbalaei and Rajyashree (2010); Mehrdad et al. (2012) እና Hwang et al. (2019) እንዲሁም ተዛምዷዊ ንድፍን ተከትለው በተላውጦዎች መካከል ግንኙነት የለም ካሉት የTobing (2013) ጥናቶች ጋራ የተቃረነ ነው፡፡

ነገርግን እነዚህ ጥናቶች በአተገባበራቸው ሲታዩ Karbalaei and Rajyashree (2010) የተጠቀሙት የልምምድ ጊዜ ከኹለት ወር ከፍ ቢል፣ ስለብልሃቱ አጠቃቀምም ቀጥተኛ ገለጻ ቢሰጡ፣ ጥቅም ላይ የዋለው የብልሃት ሞዴልም (Kintsch and van Dijik ,1979) የጥቅልነት ወይም የረቂቅነት ባሕርይ የሚታይበት በመሆኑ የተሻሻሉትን ቢተገብሩ ውጤቱ ሊለወጥ ይችላል፡፡ የMehrdad et al. (2012) ጥናት ደግሞ ተማሪዎች መርጠው እንደፍላጎታቸው እንዲጠቀሙ ያቀረቧቸው አዕምሯዊ የማንበብ ብልሃቶች ማጠቃለልን ጨምሮ መብዛታቸው (20) ተማሪዎች በግል ምርጫቸው ሲማሩ ትብብራዊውን ልምምድ ሊቀንሰው ይችላል፤ በማንበብ ጊዜ ትኩረት ያደረጉባቸው ይዘቶችም ቃላትና ሰዋስው ባይሆኑና ዋና ዋና ሐሳቦችና ጠቃሚ ዝርዝር ሐሳቦች ቢሆኑ ውጤታማ ሊሆን ይችላል፡፡ የHwang et al. (2019) ጥናት ደግሞ የብልሃት ልምምዱ ከክፍል ውጭ መማር ጋራ ተቀናጅቶ መሰጠቱ እንዲሁ ትብብራዊ የሆነውን የመማር ደረጃ ሊያሳጣ ይችላል፡፡ ጽንሰሐሳባዊ የማጠቃለል ብልሃቱም በሁሉም ምንባብ ዓይነቶች በተመሳሳይ ሁኔታ ላይተገበር ይችላል፡፡ አንብቦ በመረዳት ፈተና የምንባብ ምርጫውና የጥያቄ ብዛት በቅድመ (ሥዕላዊና ተራኪ ምንባቦች፣ 17 ምርጫና ሦስት አጭር መልስ ስጥ)ና ድኅረትምህርት (መረጃ ሰጭና ተራኪ ምንባቦች፣ 15 ምርጫና አምስት አጭር መልስ) መለያየቱ፣ ወይም ተመሳሳይ ቅርጽ፣ ይዘት፣ ስልትና ብዛት ያላቸው ጥያቄዎች ከተመሳሳይ (አቻ) ምንባብ አለመዘጋጀታቸው አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩበት ይችላሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች ቢስተካከሉ ውጤቱ በተቃራኒው ሊሆን ይችላል፡፡ የTobing (2013) ጥናት ተዛምዷዊ እንደመሆኑም የናሙና መጠኑ ከ138 ከፍ ቢል አጠቃላይ የማንበብ ብልሃቶች በአንብቦ መረዳት ላይ የሚኖራቸው የትንበያ ድርሻ ከፍ ሊል ይችላል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት በማጠቃለል የማንበብ ብልሃቱ ለሰባተኛ ክፍል አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች በቀጥታ፣ በልሥራ፣ እንሥራ፣ ሥሩ ሞዴል፣ በቡድንና በግል መር በሆነ የልምምድ አቀራረብ ተተግብሮ ውጤታማ መሆኑ ታውቋል። ቀደምት ጥናቶችም ብልሃቱን በተለያየ የጥናት ንድፍ፣ በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች፣ በአንደኛም ሆነ በኹለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ተግብረው አንብቦ መረዳትን ውጤታማ ሊያደርግ እንደሚችል ጠቁመዋል።

## 6. ማጠቃለያ መደምደሚያና የመፍትሔ አስተያየቶች

ይህ ጥናት የማጠቃለል ብልሃትን ተጠቅሞ ማንበብን መማር፤ በአማርኛ አፍፈት የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ፤ ለመመርመር የተካሄደ ነበር። ለዚህም በጎንደር ከተማ አስተዳደር በአጼ በካፋ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤት የ2015ዓ.ም. የ7ኛ"1" ተማሪዎች የሙከራና የ7ኛ"3" ተማሪዎች ደግሞ የቁጥጥር ምድብ ሆነው ለ12 ሳምንት በጥናቱ ተሳትፈዋል። ትምህርቱም በአጥኚው ስልጠና በተሰጣት የክፍል ደረጃው መምህርት አማካይነት ተሰጥቷል። ትምህርቱም በምልከታና ቃለመጠይቅ ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎበታል። በመጨረሻም ድኅረትምህርት መረጃው ተሰብስቧል።

ቅድመትምህርትና ድኅረትምህርት በተገኙ መረጃዎች መነሻነትም የጥናቱ መላምት ምላሽ አግኝቷል። ከአበርተኮር መዋቅራዊ ትንተና ሞዴሉ ውጤት እንደተስተዋለውም የማጠቃለል ብልሃት አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ ጉልህ አዎንታዊ ቀጥተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። ከዚህ በመነሳትም መደምደሚያዎችና የመፍትሔ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል።

የዚህ ጥናት የመረጃ ትንተና ውጤት እንዳመለከተውም የማጠቃለል ብልሃትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ቀጥተኛ ግንኙነት ታይቶባቸዋል።

ውጤቱም ከሥነትምህርት አንጻር ሲታይ ብልሃቱን በግልጽ ማስተማር ውጤታማ ያደርጋል። በመሆኑም መምህራንም በሚያስተምሩበት መጽሐፍ ውስጥ በኢቀጥታ አቀራረብ የተካተቱ በማጠቃለል የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት መተግበር/ መጠቀም እንዳለባቸው ማስተዋል አለባቸው የሚል አንድምታም አለው። በመማሪያ መጽሐፉ በኢቀጥታ ለቀረቡ በማጠቃለል የማንበብ ብልሃቶችንም የሥርዓተትምህርት አዘጋጆች የብልሃቶችን መመሪያዎች/ መርሆች ለመምህራን በስልጠና መልክ ማቅረብ፣ ወደፊትም በዝግጅት ጊዜ በትምህርት መሣሪያው ቀጥተኛው አቀራረብ ቢተኮርበት የሚል አንድምታም አለው።

ከምርምር አንጻርም ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢ የተላውጦዎች ተጽዕኗዊ ግንኙነት በስፋት አልተዳሰሰም፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በጎንደር ከተማ መሃል የሚገኝ ትምህርትቤት ነበር፤ በመሆኑም የዚህን ጥናት ውጤት ይበልጥ አረጋግጦ ለተፈለገው ሥነትምህርታዊ ተግባር ለማዋል በሌሎች ቦታዎች ተጨማሪ ጥናቶችን በማድረግ የዳበረ መረጃ ማቅረብ ይገባል፤ የሚል አድምታም አለው፡፡

ከተገኘው ውጤትም የሚከተሉት ሥነትምህርታዊና ምርምራዊ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡

1. የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል ብልሃቱን በግልጽ ማስተማር (በጥናቱ በተተገበረበት መልክ) አንብቦ በመረዳት ክፍል ውስጥ ቢተገበር ተገቢ ነው፡፡
2. የሥርዓተትምህርት አዘጋጆች ስለብልሃቱ ምንነት፣ ደረጃዎችና አላባዎች (መመሪያዎች) በመማሪያ መጻሕፍት ቢያካትቱ ለአስተማሪም ሆነ ለተማሪ ስኬት ተገቢ ሊሆን ይችላል፡፡
3. ጥናቱ በቀጣይ በሌሎች አገሮች እንደተፈተሸው ከችሎታ፣ ከጾታ፣ ከመማር እክል፣ ከማኅበረኢኮኖሚያዊ ዳራ ልዩነቶች አንጻር ብልሃቱ ይበልጥ ለየትኞቹ ውጤታማ እንደሆነ በምርምር ቢፈተሽ ተገቢ ነው፡፡
4. ጥናቱ በሰባተኛ ክፍል በአንድ ትምህርትቤት ደረጃ ብቻ የተተገበረ በመሆኑ ወደፊት በሌሎች የክፍል ደረጃዎችና ትምህርትቤቶች መፈተሽ ተገቢ ነው፡፡

**ምስጋና**

ይህ ጥናት በማከናወን ረገድ መረጃ በመስጠት፣ የሙከራ ትምህርቱን በመተግበር ለተባበሩን የአጼ በካፋ አንደኛ ደረጃ የሰባተኛ 1ና 3 ክፍል ተማሪዎችና ለክፍሉ የአማርኛ መምህርት ከፍ ያለ ምስጋና አለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የጥናቱን ረቂቅ በመገምገም ገንቢ አስተያየት ለሰጡን ዶር. ምሳዬ ሙላቴና መንግስቴ ሺፈራው(ረ/ፕ በእንግሊዝኛ) ልባዊ ምስጋና አለን፡፡ ይህን ጥናት በባጀት ድጋፍ ላደረገው የጎንደር ዩኒቨርሲቲም ከፍ ያለ ምስጋና ለማቅረብ እንወዳለን፡፡

**ዋቢዎች**

ማስተዋል ውበቱ። (2011)። *የትብብር ብልሃታዊ ማንበብ ዘዴ የአማርኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ፣ የማንበብ ተነሳሶትና የትብብር ክሂል የማሳደግ ፋይዳ፤* በሰባተኛ ክፍል ተተኳሪነት። [የሶስተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናት]። ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፤ ባህርዳር።

ታደሰ ዳርገው። (2012)። *የራስመር መማር ብልሃቶች (Self-regulated learning strategies) አንብቦ የመረዳት ችሎታን፣ የማንበብ ተነሳሽነትንና የብልሃቶችን አጠቃቀም የማሳደግ ሚና፤ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት።* [የሶስተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናት]። ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፤ባህርዳር።

ትምህርት ሚኒስቴር። (2007)። *አማርኛ እንደአፍመፍቻ ቋንቋ የሰባተኛ ክፍል የተማሪ መጽሐፍ።* አል-ጉሬር አሳታሚ ድርጅት (ዱባይ)ና ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ። Nova publications, Jalandhar-Delhi, works@nppl.in

አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርትቢሮ። (2015)። *አማርኛ እንደአፍመፍቻ ቋንቋ የሰባተኛ ክፍል የተማሪ መጽሐፍ።* የምሁራን መማክርት ጉባዔ ትብብር የተዘጋጀ። ባሕርዳር።

Aghaie, R., & Zhang, L. J. (2012). Effects of explicit instruction in cognitive and metacognitive reading strategies on Iranian EFL students' reading performance and strategy transfer. *Instructional Science*, *40*(6), 1063-1081. DOI 10.1007/sl 1251-01 1-9202-5

Al-Darayseh, A. (2014). The Impact of Using Explicit/Implicit Vocabulary Teaching Strategies on Improving Students' Vocabulary and Reading Comprehension. *Theory & Practice in Language Studies*, *4*(6).

Alexander, P. A., & Fox, E. (2004). A historical perspective on reading research and practice. *Theoretical models and processes of reading*, 5, 33-68.

Al-Momani, A., Hussin, S., & Hamat, A. (2014). In the Light of Reading Strategies Comprehension improvement (Text Book, Online Material and Smartphone Application). *Arab World English Journal*.

Antoni Nurman. 2010. Exploring EFL Teachers" Strategies in Teaching Reading Comprehension. *Journal Penelitian Pendidikan.* 11(2):39-51.

Bahrami, S., and Rahimy, R.(2022). Effect of Backward Summary Technique on Reading Comprehension Enhancement among Non-English Majors. *HOW Journal* 29, no. 1 (2022): 154-172.

Ballou (2012).Using Explicit Strategy Instruction to Improve Reading Comprehension.

Barber, A. T., & Klauda, S. L. (2020). How reading motivation and engagement enable reading achievement: Policy implications. *Policy Insights from the Behavioral and Brain Sciences*, 7(1), 27-34. DOI: 10.1177/2372732219893385

Barreiro Cedeño, J. P. (2019). *Improving Reading Comprehension of Narrative Texts through Summaries* (Master's thesis, Universidad Casa Grande. Departamento de Posgrado).

Bean, T. W., & Steenwyk, F. L. (1984). The effect of three forms of summarization instruction on sixth graders' summary writing and comprehension. *Journal of Reading Behavior*, 16(4), 297-306. https://journals.sagepub.com/doi/abs/10.1080/10862968409547523

Braxton, D. M. (2009). *The effects of two summarization strategies using expository text on the reading comprehension and summary writing of fourth-and fifth-grade students in an urban, title 1 school* [Doctoral dissertation].

Brown, A. L., Day, J. D., & Jones, R. S. (1983). The development of plans for summarizing texts. *Child development*, 968-979.


Brown, A. L., Day, J. D., & Jones, R. S. (1983). The development of plans for summarizing texts. *Child development*, 968-979.


Brown, A. L., & Day, J. D. (1983). Macrorules for summarizing texts: The development of expertise. *Journal of verbal learning and verbal behavior*, 22(1),1-14.https://www.sciencedirect.com/science/article/pii/S0022537183800024

Brown, S. A. (2018). The Effects of Explicit Main Idea and Summarization Instruction on Reading Comprehension of Expository Text for Alternative High School Students(2018). *All Graduate Theses and Dissertations*. 7134. https://digitalcommons.usu.edu/etd/7134

Butler, S., Urrutia, K., Buenger, A., & Hunt, M. (2010). A review of the current research on comprehension instruction. *Contract No. ED-08-CO0123). National Reading Technical Assistance Center, RMC Research Corporation. Retrieved from US Department of Education http://www2. ed. gov/programs/readingfirst/support/compfinal. pdf.*

Chang, K. E., Sung, Y. T., & Chen, I. D. (2002). The effect of concept mapping to enhance text comprehension and summarization. *The Journal of Experimental Education*, *71*(1), 5-23.

Chiu, C. H. (2015). Enhancing reading comprehension and summarization abilities of EFL learners through online summarization practice. *The Journal of Language Learning and Teaching*, 5(1), 79-95. http://www.jltl.org/jltl/

Cho, Y. (2012). *Teaching summary writing through direct instruction to improve test comprehension for students in ESL/EFL classroom* [Doctoral dissertation, University of Wisconsin-River Fall].

Corder-Ponce,W.L. (2000). Summarization interaction: Effects on foreign language comprehension and summarization of expository texts. *Reading Research and Instruction*, 39(4), 329-350. https://doi.org/10.1080/19388070009558329

Duke, N. K., & Pearson, P. D. (2009). Effective practices for developing reading comprehension.

Durkin, D. (1978). What classroom observations reveal about reading comprehension instruction. *Reading Research Quarterly*, *14*, 481–533.

Early Grade Reading Assessment. (2010). *Ethiopian early grade reading assessment: Data analytic report: Language & early learning.* Addis Ababa (USAID/Ethiopia).

Early Grade Reading Assessment. (2018). *Ethiopian early grade reading assessment: Data analytic report: Language & early learning*. Addis Ababa (USAID/Ethiopia).

El-Koumy, A. S. (2016). Teaching English as a foreign language to students with learning disabilities at the intermediate and advanced levels: a multiple-strategies approach. *Revised Edition (February 20, 2020). Published by Dar An-Nashr for Universities, Cairo, Egypt, Revised Edition*.

Gelati, C., Galvan, N., & Boscolo, P. (2014). Summary writing as a tool for improving the comprehension of expository texts: An intervention study in a primary school. In G. Rijlaarsdam_(Series Ed.) & P.D. Klein, P. Boscolo, L.C. Kirkpatrick, & C. Gelati (Vol. Eds.), *Studies in Writing*: *Vol. 28, Writing as a learning activity* (pp. 191–216). Leiden: Brill.

Grabe, W. (2009). Reading in a second language: *Moving from theory to practice*. Ernst Klett Sprachen.

Graham, S., & Hebert, M. (2010). *Writing to read: Evidence for how writing can improve reading:* A report from Carnegie Corporation of New York.

Hare, V. C., & Borchardt, K. M. (1984). Direct instruction of summarization skills. *ReadingResearch Quarterly*, 62-78. URL: https://www.jstor.org/stable/747652

Harris, Z. S. (1952). Discourse Analysis. *Linguistic Society of America*. https://about.jstor.org/terms.

Hashim, N. H.(2014). Assessment of a Reading Comprehension Instrument as It Relates to Cognitive Abilities as Defined by Bloom's Revised Taxonomy. *Current Issues in Education Vol. 17(1),1-15.*

Hutchins, J. (1987). Summarization: Some problems and methods. *Meaning: The frontier of informatics*, *9*, 151-173.

Hwang, G. J., Chen, M. R. A., Sung, H. Y., & Lin, M. H. (2019). Effects of integrating a concept mapping-based summarization strategy into flipped learning on students' reading performances and perceptions in Chinese courses. *British Journal of Educational Technology*, *50*(5), 2703-2719. https://doi.org/10.1111/bjet.12708

Izquierdo, A., & Jiménez, S. (2014, October). Building up Autonomy Through Reading Strategies. *PROFILE (Issues in Teachers' Professional Development)*, *16*(2), 70-72. Retrieved from http://www.redalyc.org/articulo.oa?id=169232511006

Karbalaei, A., & Rajyashree, K. S. (2010). The impact of summarization strategy training on university ESL learners' reading comprehension. *The International Journal of Language Society and Culture*, *30*, 41-53.URL: www.educ.utas.edu.au/users/tle/JOURNAL/

Khoshnevis, I., & Parvinnejad, S. (2015). The effect of text summarization as a cognitive strategy on the achievement of male and female language learners' reading comprehension. *International Journal of Learning and Development*, 5(3), 57-75. DOI: https://doi.org/10.5296/ijld.v5i3.8271

Khoshnevis, I. (2015). The Effect of Text Summarization as a Cognitive Strategy on the Achievement of Male and Female Language Learners' Reading Comprehension.

Kintsch, W., & Van Dijk, T. A. (1978). Toward a model of text comprehension and production. *Psychological review*, 85(5), 363.

Indillah, Y. (2020). *An Analysis of Reading Comprehension Question By Using Revised Bloom's Taxonomy through Quizizz Application* [Doctoral dissertation].

Lau, K. L., & Chan, D. W. (2007). The effects of cognitive strategy instruction on Chinese reading comprehension among Hong Kong low achieving students. *Reading and Writing*, *20*(8), 833-857.

Lawshe, C. H. (1975). A quantitative approach to content validity. *Personnel psychology*, *28*, 563–575.

Liu, F. (2010). A Short Analysis of the Nature of Reading. *English Language Teaching*, 3(3), 152-157.

Marzano, R. J., Pickering, D., & Pollock, J. E. (2001). *Classroom instruction that works: Research-based strategies for increasing student achievement*. Ascd.

Maxwell, L. (2014). Implicit vs.Explicit Instructional Strategies Regarding Reading Comprehension.https://archives.northwestu.edu/bitstream/handle/nu/25699/maxwell_lisa_med_2014_07.pdf?sequence=1&isAllowed=y

Mehrdad, A. G., Ahghar, M. R., & Ahghar, M. (2012). The effect of teaching cognitive and metacognitive strategies on EFL students' reading comprehension across proficiency levels. *Procedia-Social and Behavioral Sciences*, *46*, 3757-3763.

Ministry of Education. (2018). *Ethiopian Education Development Roadmap (2018-30).* Addis Ababa, Ethiopia.

National Reading Panel (US), National Institute of Child Health, Human Development (US), National Reading Excellence Initiative, National Institute for Literacy (US), United States. Public Health Service, & United States Department of Health. (2000). *Report of the National Reading Panel: Teaching children to read: An evidence-based assessment of the scientific research literature on reading and its implications for reading instruction: Reports of the subgroups.* National Institute of Child Health and Human Development, National Institutes of Health.

Nelson, J. R., Smith, D. J., & Dodd, J. M. (1992). The effects of teaching a summary skills strategy to students identified as learning disabled on their comprehension of science text. *Education and Treatment of Children*, 228-243.

Özdemir, S. (2018). The effect of summarization strategies teaching on strategy usage and narrative text summarization success. http://acikerisim.bartin.edu.tr/handle/11772/1676

Pardede, P. (2008). A Review on Reading Theories and its Implication to the Teaching of Reading. *UKI: ELT'n Edu~ A cyber ELT & Edu service from Universitas Kristen Indonesia*.

Pečjak, S., & Pirc, T. (2018). Developing Summarizing Skills in 4th Grade Students: Intervention Programme Effects: Intervention programme effects. *International Electronic Journal of Elementary Education*, *10*(5), 571-581. DOI: 10.26822/iejee.2018541306

Robinson, R., & Good, T. L. (1987). *Becoming an effective reading teacher*. New York: Harper & Row.

Sabatini, J. Bruce, K. and Steinberg, J.(2013). SARA Reading Components Tests, RISE Form: Test Design and Technical Adequacy. *ETS Research Report Series,* listening, learning,leading.

Savolainen, R. (2018). Self-determination and expectancy-value: Comparison of cognitive psychological approaches to motivators for information seeking about job opportunities. *Aslib Journal of Information Management*. https://doi.org/10.1108/AJIM-10-2017-0242.

Schunk, D. H. (1996). Learning theories. *Printice Hall Inc., New Jersey*, *53*.

Snowling, M. J., & Hulme, C. E. (2005). *The science of reading: A handbook.* Blackwell Publishing.

Solikhah, N. A., & Sari, R. A. (2022). The Influence of Summarizing Short Stories Towards Students' Narrative Writing Ability. *Journal Corner of Education, Linguistics, and Literature*, *1*(3), 176-190.

Taki, Y. (2017). Effects of Explicit and Implicit Strategy Instruction on Reading Strategies. *松山大学論集*, 29(5), 25-48.

Talebi, M., & Talebi, M. (2015). The Effect of Teaching Critical Reading Strategies on Making Advanced Iranian EFL Learners the Critical Readers. *Cumhuriyet Üniversitesi Fen Edebiyat Fakültesi Fen Bilimleri Dergisi*, *36*(3), 1179-1189.

Tiruneh, D. T. (2014). The effect of explicit reading strategy instruction on reading comprehension of upper primary grade students. *International Journal of Education*, 6(3), 81.

Tobing, I. R. A. (2013). *The relationship of reading strategies and self-efficacy with the reading comprehension of high school students in Indonesia* [Doctoral dissertation, University of Kansas].

Wegner, C., Minnaert, L., & Strehlke, F. (2013). The Importance of Learning Strategies and How the Project" Kolumbus-Kids" Promotes Them Successfully. *European Journal of Science and Mathematics Education*, *1*(3), 137-143.

Weibell, C. J. (2011). *Principles of learning: A conceptual framework for domain-specific theories of learning*. Brigham Young University.

Westby, C., Culatta, B., Lawrence, B., & Hall-Kenyon, K. (2010). Summarizing expository texts. *Topics in Language Disorders*, *30*(4), 275-287.

Wormeli,R. (2019). *Summarization in Any Subject. 60 Innovative, Tech-Infused Strategies for Deeper Student Learning,* 2nd Edition.

Wormeli, R. (2005). *Summarization in any subject: 50 techniques to improve student learning*. Alexandria, VA: Association for Supervision and Curriculum Development.

Zhang, L. J., Gu, P. Y., & Hu, G. (2008). A cognitive perspective on Singaporean primary school pupils' use of reading strategies in learning to read in English. *British Journal of Educational Psychology*, *78*(2), 245-271.